ספריית פיג'מה

# המשך פעילויות בעקבות הסיפור - የሲማቺ ታላቁ ቀን

በ: ኢሪስ ኤሊያሁ ኮሄን
ምሳሌዎች: ሌላኽ ሃበርማን
הוֹצָאָה: טל מאי
የእድሜ ክልል: ሁለተኛ ክፍል

קְרִיאָה

## ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር

ታላቁ የሲማቺ ቀን” ረዘም ያለ መጽሐፍ ነው። ለዚያም ነው በሁለት ክፍሎች ለማንበብ የሚመከረው:- ሲማቺ“ ወንድሟ አብራም ለምን የበዓል ልብስ እንደለበሰ ከተገረመች በኋላ ማንበብ ያቁሙና በሚቀጥለው ቀን ማንበብዎን ይቀጥሉ።

שִׂיחָה

## ትዝታዎች

በመጽሐፉ ውስጥ አያቱ የልጅነት ጊዜዋን ትዝታ ትተርካለች። ይህ ለእናንተ ለወላጆች ከልጅነታችሁ ጀምሮ ልዩ ጊዜዎችን እንድታካፍሉ እድል ነው። ስላደረጋችኋቸው ነገሮች፣ ከዚህ በፊት ማድረግ እችላለሁ ብላችሁ ያላሰባችሁትን ወይም በእናንተና በወንድሞቻችሁ መካከል ስላለው ግንኙነት ተርኩ። እንዲሁም ልጆቹን ጠይቋቸው:- ወደ ኋላ ?በመመልከት በራሳቸው ባገኙት ችሎታ ያስደነቋቸውን ያደረጓቸውን ልዩ ድርጊቶች ማስታወስ ይችላሉ

שֵׁמַע

## ሲማቺን ማዳመጥ

ታሪኩ እንዴት ይሰማል? ኮዱን ስካን ማድረግ መጽሐፉን እያገላበጡ ታሪኩን ለማዳመጥ እንዲችሉ ይመራዎታል።

מִשְׂחָק

**አናናስ በራስ ላይ**

አብራምና ኔሚ አናናስ ራሳቸው ላይ በማድረግ የመራመድ ጨዋታ ይጫወታሉ። ማን እንደማይጥልም ለማየት ይወዳደራሉ። ተመሳሳይ ጨዋታም መጫወት ትችላላችሁ፡- በራሳችሁ ላይ የምታስቀምጧቸውን ዕቃዎች – ትራስ፣ አሻንጉሊት ወይም ሳጥን ምረጡና፡- ከመካከላችሁ በመራመድ ራሱ ላይ መሸከም የሚችለው ማነው? እስከ ምን ርቀት? የሚለውን አረጋግጡ።

מִשְׂחָק

**ባህሩን ተከትሎ**

ታሪኩ ከባህር ጋር የተያያዙ ብዙ ተግባራትን ይገልፃል፡- የዓሳ እንቅስቃሴ፣ ጀልባ መቅዘፍ፣ ዋና፣ የዓሣ ማጥመጃ መረቦችን መሰብሰብ፣ በመርከብ ምሰሶ ላይ ባንዲራ ማውለብለብ ወይም መስቀል። ከድርጊቶቹ ውስጥ አንዱን በመምረጥ በእንቅስቃሴ ማሳየት ትችላላችሁ። የቤተሰቡ አባላት የትኛውን ድርጊት እንደፈለጉ መገመት የሚኖርባቸው !ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት ምስሎች ውስጥ የሚፈልጉት ይሆናል። መልካም እድል

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

ለተጨማሪ ስራዎች፣ መዝሙሮችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org